**የኖርዌይኛ ቋንቋ ፈተና፣ የህብረተሰብ ትምህርት ፈተና እና/ወይም የኖርዌይ ዜግነት ፈተና ተፈታኞች ግላዊ መረጃዎች አያያዝ መግለጫ**

# 1. የኖርዌይኛ ቋንቋ ፈተና፣ የህብረተሰብ ትምህርት ፈተና እና/ወይም የኖርዌይ ዜግነት ፈተና ተፈታኞች ግላዊ መረጃዎች አያያዝ

የኖርዌይኛ ቋንቋ ፈተና፣ የህብረተሰብ ትምህርት ፈተና እና/ወይም የኖርዌይ ዜግነት ፈተና ለመፈተን ሲያመለክቱ ግላዊ መረጃዎቻችን እንይዛለን። የግላዊ መረጃዎቹ አይነት፥ ለምን መያዝ እንዳስፈለገን እና እንዲሁም አያያዙን በተመለከተ የእርሶ መብቶችን ለመረዳት ከታች የሰፈረውን ጽሁፍ ያንብቡ።

የመረጃዎች ያዥ የኖርዌይ ከፈተኛ ትምህርት እና ብቃት ዳይሬክቶሬት ነው። ይህ ማለት ዳይሬክቶሬቱ የእርሶን ግላዊ መረጃዎች አያያዝ እና አጠቃቀም በተመለከተ ኃላፊነቱን ይወስዳል።

# 2. የእርሶን ግላዊ መረጃዎች መያዝ ያስፈለገበት ምክንያት

ከዓላማችን ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስራዎች ለማከናወን አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፥ ጥንቃቄ የሚጠይቁ የግል መረጃዎችን ጨምሮ ስለ እናንተ የግል መረጃዎችን እናሰባስባለን። የእኛ ዓላማ ፍልሰተኞች በኖርዌይ ኅብረተሰብ ውስጥ መሳተፍ እንዲችሉ የሚረዳ እውቀትና ክህሎት መስጠት፥ እንዲሁም ደግሞ የኖርዌይኛ ቋንቋ እና የኅብረተሰብ ዕውቀት ችሎታቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ ፈተና ማስወሰድ ነው።

ይህ ተግባራዊ የሚሆነው በGDPR አንቀጽ 6 ቁጥር 1 e) እና የማዋሃድ ህግ አንቀጽ 41(1) b) እና/ወይም c) እንዲሁም የማዋሃድ ድንጋጌ አንቀጽ 54 መሰረት ነው። ጥንቃቄ የሚጠይቁ ግላዊ መረጃዎች አያያዝ GDPR አንቀጽ 9 ቁጥር 2 ፊደል g) እና የማዋሃድ ህግ አንቀጽ 41(1) b) እና/ወይም c)ን መሰረት ያደረገ ይሆናል። በሌላ አገላለጽ ፈተና ሲወስዱ ከታች (ቁጥር- 4) የተዘረዘሩትን የእርስዎ ግላዊ መረጃዎችን የመያዝ ህጋዊ የሆነ መብት እና ግዴታ አለብን።

ግላዊ መረጃዎችን የምንሰበስበውና እና የምንጠቀመው የሚከተሉትን ስራዎች ለማከናወን ስለሚረዳን ነው:

- የኖርዌይኛ ቋንቋ ፈተና፣ የህብረተሰብ ትምህርት ፈተና እና/ወይም የኖርዌይ ዜግነት ፈተናን ማካሄድ እና የፈተና ጥራቱን ማረጋገጥ
- በመፈተኛ ቦታው ተፈታኞችን ማስተናገድ

- ይግባኝ የሚቀርብባቸው ውሳኔዎች ላይ ይግባኝ የመጠየቅ መብቶን መጠበቅ
- የስታትስቲክስ (አሃዛዊ መረጃዎች ጥናት)
- የምርምር ጥናት እና ትንተና ማካሄድ

ኖርዌይኛ ቋንቋን የማንበብ እና የማዳመጥ ፈተና፣ የህብረተሰብ ትምህርት ፈተና እና የኖርዌይ ዜግነት ፈተና አርሞ ውጤት ለመስጠት፥ የማዋሃድ ህግ አንቀጽ 41(1) c) እና የማዋሃድ ድንጋጌ አንቀጽ 64ን መሰረት ያደረጉ አውቶማቲክ (የኮምፒዩተር) ውሳኔዎችን እንጠቀማለን።

የሶስቱ ፈተናዎች አይነት የምርጫ ጥያቄዎችን የያዙ ሲሆኑ እያንዳንዱ ጥያቄ አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ ይኖረዋል። የትኞቹ መልሶች ትክክል እንደሆኑ እና የፈተና ማለፊያው ነጥብ ስንት መሆን እንዳለበት በኮምፒዩተር መፈተኛ ስርዓቱ ውስጥ አስቀድሞ የተወሰነ ነው። ተፈታኙ በትክክል የመለሳቸው መልሶች እያንዳንዳቸው አንድ ነጥብ የሚያሰጡ ሲሆን፥ የነጥቦቹ ድምር የተፈታኙ ውጤት ይሆናል። ውጤቱ ተፈታኙ ማለፍ ወይም አለማለፉን ያሳያል።

የኖርዌይኛ ቋንቋ የጽሑፍ እና የንግግር ፈተና የሚታረመው እና ዉጤት የሚሰላው በኮምፒዩተር ሳይሆን በሰዎች ነው።

የከፍተኛ ትምህርትና ብቃት ዳይሬክቶሬቱ አውቶማቲክ (የኮምፒዩተር) ውሳኔዎችን ሰዎች እንዲያዩ እና እንዲከታተሉ ሊያደርግ ይችላል። የቴክኒክ ወይም ሌላ ስህተት ሊኖር እንደሚችል የሚጠቁሙ ጥርጣሬዎች ወይም ሁኔታዎች ካሉ የከፍተኛ ትምህርትና ብቃት ዳይሬክቶሬቱ የፈተናው ስርዓት እና አካሄድን ከፍቶ ይመረምራል።

# 3. ግላዊ መረጃዎችን ከየት እናሰባስባለን?

ግላዊ መረጃዎችን የምንሰበስበው ከእርስዎ እና ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ነው። ከነዚህ የመንግስት መስሪያ ቤቶች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው:

- የማዋሃድ እና ብዝሃነት ዳይሬክቶሬት (IMDi)
- ኮሚዩነዎች (ወረዳዎች)/የፈተና ቦታዎች
- የአውራጃ መሪ (የይግባኝ ጉዳይ ለበላይ አካል ሲቀርብ)
- የኖርዌይ ኢሚግሬሽን ዳይሬክቶሬት (UDI)
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
- የኖርዌይ የወሳኝ ኩነቶች ጽ/ቤት

## 4. የምንይዛቸው ግላዊ መረጃዎች አይነት

እርስዎን በተመለከተ የምንሰበስባቸው እና የምንይዛቸው ግላዊ መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው።

- ስም
- አድራሻ
- የስልክ ቁጥር
- ኢሜይል
- የትውልድ ቀን
- የመታወቂያ ቁጥር
- የDUF ቁጥር
- ጊዜያዊ የመታወቂያ ቁጥር
- የፓስፖርት ቁጥር
- የተፈታኝ ቁጥር
- ፆታ
- የፈተና ምላሾች
- የፈተና ውጤት
- የፈተና አይነት
- ፈተና የተወሰደበት ቀን እና ሰዓት
- ፈተናው የተወሰደበት ቋንቋ*
- የፈተና ቦታ
- የይግባኝ ጥያቄ
- ልዩነት (ዝባት)
- ማጭበርበር

በተጨማሪም ከፌብርዋሪ 15 2022 ዓ.ም በፊት በዚህ መረጃ ለተመዘገቡ ተፈታኞች የሚከተሉትን የግል መረጃዎች እንይዛለን።

- የትውልድ ሃገር*
- የአፍ መፍቻ ቋንቋ*

* እነዚህ ጥንቃቄ የሚጠይቁ ግላዊ መረጃዎች ተብለው ይታሰባሉ።

## 5. ግላዊ መረጃዎችን ለሌሎች አሳልፎ ስለመስጠት

የከፍተኛ ትምህርትና ብቃት ዳይሬክቶሬቱ የእርሶን ግላዊ መረጃዎች በህግ ካልተጠየቀ በስተቀር ለሌሎች አሳልፎ አይሰጥም። ህጋዊ ሽፋን ያለው ውሳኔ ግላዊ መረጃን አሳልፎን እንድሰጥ ከሚያስገድዱን ምሳሌዎች አንዱ ሊሆን ይችላል።

ብሔራዊ መታወቂያ ቁጥር ካሎት የፈተናዎን ውጤት እና ተያያዥ ግላዊ መረጃዎችን በ **ሰርቲፊኬት መዝገብ** ውስጥ በመግባት ያገኛሉ።

የከፍተኛ ትምህርትና ብቃት ዳይሬክቶሬቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት የእርሶን ግላዊ መረጃዎች አሳልፎ ከሚሰጣቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል:

- የማዋሃድ እና ብዝሃነት ዳይሬክቶሬት (IMDi)
- ኮሚዩነዎች (ወረዳዎች)/የፈተና ቦታዎች
- የአውራጃ መሪ (የይግባኝ ጉዳይ ለበላይ አካል ሲቀርብ)
- የኖርዌይ ስታትስቲክስ ቢሮ
- የኖርዌይ ኢሚግሬሽን ዳይሬክቶሬት (UDI)
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
- ሲክት (Sikt)

የከፍተኛ ትምህርትና ብቃት ዳይሬክቶሬት ግላዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለማከማቸት ወይም በሌላ መልኩ ለመያዝ የመረጃ አያያዝ ባለሙያዎችን ይጠቀማል። ይህን ስናደርግ በሁሉም የሂደት ደረጃዎች ላይ የመረጃ ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚረዳ ስምምነት ከባለሙያዎቹ ጋር ተፈራርመናል። በአሁኑ ወቅት የሚከተሉትን የመረጃ አያያዝ ባለሙያዎችን እንጠቀማለን።

- Enovate AS

የግላዊ መረጃዎች አያያዝ ስራዎቻችን በሙሉ የምናካሂደው በአውሮፓ ህብረት/አውሮፓ የኢኮኖሚ ቀጠና አባል ሃገራት ውስጥ ነው።

## 6. ግላዊ መርጃዎችን የምንይዝበት የግዜ ርዝመት

ግላዊ መረጃዎ እኛ ጋር የሚቆየው የማዋሃድ ህጉ አንቀጽ 41 ቁጥር 1 ላይ ለሰፈሩት ዓላማዎች አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ነው። የማዋሃድ ድንጋጌ አንቀጽ 60 ቁጥር አምስት እንደሚገልጸው የተፈታኝ ግላዊ መረጃ ፈተና ከወሰደበት ቀን ጀምሮ ለ20 ዓመታት ያህል ሊቀመጥ ይችላል። ስለዚህ ግላዊ መረጃዎችን እስከ 20 ዓመታት ልናስቀምጥ እንችላለን። ከ 20 ዓመት በኋላ ግላዊ መረጃዎችን እንደመስሳለን።

የሚከተሉት መረጃዎች ለአጭር ጊዜ ይቀመጣሉ

- አድራሻ ለ 2 ዓመት ይቀመጣል
- በደረጃ C1 የሚሰጥ የንባብ መረዳት ችሎታ ፈተና እና የቃል ፈተና የድምፅ ቅጂ ለ 1 አመት ይቀመጣል
- የክፍያ ሁኔታ መረጃ ለ3 ዓመት ይቀመጣል
- ጊዜያዊ እና የመጨረሻ የማጭበርበር ጉዳይ ለ 3 ዓመት ይቀመጣል

## 2. ግላዊ መረጃዎችዎ አያያዛችን በተመለከተ የእርሶ መብቶች

ግላዊ መረጃዎችን እንዲያዩ እና/ወይም እንዲስተካከልሎ የመጠየቅ መብት እና እንዲሁም ደግሞ በአንዳንድ ሁኔታዎች የግላዊ መረጃዎቾ አያያዛችን የተወሰነ እንዲሆን መጠየቅ እና የአያያዝ ሂደቱን የመቃወም መብት አሎት። ስለ ነዚህ መብቶች ይዘት **በኖርዌይ የዳታ ጥበቃ ባለስልጣን ድረ ገጽ** ላይ ማንበብ ይችላሉ።

መብቶቾን መጠቀም ከፈለጉ ኢሜይል ወደ **proveadministrasjon@hkdir.no** መላክ ይኖርቦታል። በተቻለ ፍጥነትና ከ30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ምላሽ እንሰጦታለን ።

ለጥያቄዎ ምላሽ ከመስጠታችን በፊት ማንነትዎን እንዲያረጋግጡ ወይም ተጨማሪ መረጃ እንዲሰጡን ልንጠይቅዎ እንችላለን። ይህን የምናደርገው ግላዊ መረጃዎን ከእርስዎ ሌላ ማንም ሰው እጅ እንዳይገባ እና እንዲሁም መረጃዎን እርሶን መስለው ለሚጠይቁን ሰዎች ላለመስጠት በሚል ጥንቃቄ ነው።

## 8. ግላዊ መረጃዎች ጥበቃ ኃላፊ

የከፍተኛ ትምህርትና ብቃት ዳይሬክቶሬት የራሱ የግላዊ መረጃዎች ጥበቃ ኃላፊ አለው። የኃላፊው ስም **ቶርጂር ሆቭደን** ሲሆን በኢሜይል personvernombud@hkdir.no ማግኘት ይቻላል።

## 9. ቅሬታ

የግላዊ መረጃዎች አያያዛችን እዚህ መግለጫ ላይ ከገለጽነው ጋር የማይጣጣም ወይም የግላዊ መረጃ ጥበቃ ህጎችን የጣሰ ሆኖ ካገኙት፥ ቅሬታዎን ለኖርዌይ የዳታ ጥበቃ ባለሥልጣን ሊያቀርቡ ይችላሉ።

ባላስልጣን ጽ/ቤቱን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል **የኖርዌይ የዳታ ጥበቃ ባለስልጣን ድረ ገጽ** ገብተው ማንበብ ይችላሉ።

## 10. ለውጦች

በአገልግሎቶቻችን ወይም በግላዊ መረጃ አያያዝ ህግ ላይ ለውጦች ቢደረጉ፥ የዚህ መግለጫ ይዘት ላይ ለውጦች ሊያስከትል ይችላል። በድረ-ገጻችን ላይ የምናቀርበው ይህ የግላዊ መረጃ አያያዝ መግለጫ ወቅቱን የጠበቀ ይሆናል።

## 11. እኛን ለማግኘት ሲፈልጉ

ከከፍተኛ ትምህርትና ብቃት ዳይሬክቶሬት ጋር ለመገናኘት የሚረዱ መረጃዎች:

አድራሻ: Fortunen 1, 5013 Bergen
ኢሜይል: **post@hkdir.no**
ስልክ ቁጥር: 55 30 38 00
የድርጅት መለያ ቁጥር: 974788985

ስለ ግላዊ መረጃዎ አያያዛችን ጥያቄ ካለዎት ኢሜይል ወደ **proveadministrasjon@hkdir.no** መላክ ይችላሉ።